# ‹‹ጎንደር ችግኝ ለመትከል ከኦጋዴን ሰው ይጫናልን?››

(አስማው ታደሰ)



አልማ ግንቦት 20 ቀን 1984 ዓ.ም. ተመሠረተ። ከምስረታው ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ አሜሪካ ስንዝ፣ ከእግሬ አስቀድሞ የአሜሪካን ምድር የረገጠው ሀሳቤ ነበር። የተሳፈርኩበት የአገሬ አውሮፕላን ገና የኢትዮጵያን የአየር ክልል አልፎ ሳይሻገር ጀምሮ ነው በዓይነ ህሊናዬ አሜሪካ ውስጥ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ጋር በአገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መወያየት የጀመርኩት።

ያሰብኩት አልቀረም፣ እዚያ ደርሼም በሥራ ጉብኝቴ ጣልቃና ከጉብኝቴ መጠናቀቅ በኋላ አሜሪካ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶች ጋር አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስተን ለመወያየት በቅተናል። መነጋገሪያ እንዲሆኑን በማስታወሻዬ ላይ ካሰፈርኳቸው አጀንዳዎች አንዱና ዋነኛው የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) መመስረት እንደነበር አይረሳኝም። በዚህም መሠረት፣ በዘጠኝ የአሜሪካ ከተሞች ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር የሃሳብ ልውውጥ፣ ክርክርና ንትርክ አድርገናል። በአንድ አዳራሽ ውስጥ በሺህና በመቶዎች እየተሰበሰቡም ሆነ በግልና በቡድን እየሆኑ ያገኘኋቸው በሙሉ ወይም አብዛኛዎቹ የአልማ መመሥረት ዜና ቀድሞ ያልደረሳቸው ስለነበሩ፣ የዜና ብስራቱን ያበሰርኩላቸው ኩራትና የለውጥ መንፈስ ባዘለ ስሜት ነው።

እነዚህ ወገኖች ብቅለታቸው ከኢትዮጵያ ቢሆንም፣ ነዋሪነታቸው ግን በአሜሪካ ነውና፣ የአልማን መመሥረት ጨምሮ የመነሻ ንግግር ባደረግሁባቸው ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የስክነ የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሃሳቦች ሊሰነዘሩ እንደሚችሉ አስቀድሜ መገመቴ አልቀረም።

አሜሪካ የዓለማችን ግንባር ቀደም ሃብታምና የለማች አገር ነች። ‹‹ዴሞክራሲ እጅግ ዳብሮ በሁለት እግሩ የቆመባት አገር›› እየተባለ ሲነገርላትም በተደጋጋሚ ስምቻለሁ። ይህም፣ ‹‹በዚህች አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በሚኖሩባት አሜሪካ አምሳል የተቀረፁ፣ የዴሞክራሲና የልማትን ፅንሰ ሀሳብ ጠንቅቀው ያወቁ በሳሎች ይሆናሉ›› የሚል ግምት አሳድሮብኝ ነበር። የዴሞክራሲን ‹‹ሀሁ›› መቁጠር ከጀመረችዋና ድሃ ከሆነችዋ አገሬ የሄድኩ ሰው ነኝና፣

**በሰለጠነው ዓለም ውስጥ የሚኖሩትን ‹‹ስልጡን››** ኢትዮጵያውያን የሚያስረዳ ርቱዕ አንደበትና ጥልቅ ግንዛቤ እንደሌለኝ መቁጠሬ ደግሞ በሰፊ የሀሳብ ባሕር ውስጥ እያስዋኘ ክፉኛ አጉላልቶኛል፡፡

ግምቴ የተሳሳተ መሆኑን መገንዘብ የጀመርኩት ግን የመጀመሪያዎቹን ተሰብሳቢዎች ባገኘሁ ቀን ነው፡፡ ተከታዮቹ ስብሰባዎችም ተመሳሳይ ነበሩ፡፡ አሜሪካ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አብዛኞዎቹ የሰከኑ ቢሆኑም፣ ጥቂቶች የሰከሩ መኖራቸውን ስብሰባዎቹ አስገንዝበውኛል፡፡

ከሁሉም በላይ ዓይነተ ብዙ ሀሳቦችን አስነስቶ ያነጋገረን አጀንዳ ደግሞ የአልማ ምስረታ ጉዳይ ነበር፡፡ የአልማን መመሥረት ደግፈው መልካሙን ሁሉ የተመኙለትና ከጎኑ እንደሚቆሙ ቃል የገቡለት አብዛኛውን ቁጥር ይይዛሉ፡፡



በንፁህ ልቦናቸው የተቃወሙና ለጊዜው በጥርጣሬ ዓይን እንደሚመለከቱት አስተያየታቸውን የሰጡትም ጥቂት አልነበሩም። ጥቂቶች ግን፣ ከሁሉም በፊት ከሌላው ወገን የሚነገረውን ለማድመጥ ዝግጁነት የሌላቸው ናቸው። ጥሩ አድማጭ ስላልሆኑም ጥሩ ተናጋሪ ሊሆኑ አልታደሉም። ገንቢ የሆኑትን ሁለት የድጋፍና የተቃውሞ መንገዶች የተከተሉት አብዛኛዎቹ ወገኖች እነዚህን አፍራሽ የጭፍን ጥላቻና ውግዘት ጎራ የፈጠሩትን ጥቂቶች የጨዋነት ደንብን እንዲከተሉ ያላሳሰቡበት መድረክ አልገጠመኝም። እነሱ ግን፣ በጄ ሳይሉ ቀሩ።

እናም፣ አልማን በጭራቅ አምሳል መስለው አወገዙት። ‹‹የአንድ ወገን የፖለቲካ ዓላማ ማራመጃ መሣሪያ እንጂ፣ የልማት ማህበር አይደለም›› አሉት። ከዚያም አልፈው፣ በልማት ሥም የህዝብ ንብረት ለመዝረፍ የተቋቋመ የወንበዴ ቡድን ስለመሆኑ ደምድመው ተናገሩ። በተለይም የፓስፊክ ውቅያኖስ ጠርዝ አካባቢ ከሚገኙ ሦስት ከተሞች፣ እኔ ስብሳቢው ላይም፣ ሊናገሩት ቀርቶ ሊሰሙት የሚዘገንን ፀያፍ የስድብ ናዳ ያወረዱብኝ፣ ቡጢ ሊሰነዝሩ ተጋብዘው በተቆጭና በገላጋይ ብዛት የተገቱ ገጥመውኛል። ሰሚ ጆሮ በማጣታቸው ተናደው ስብሰባውን አቋርጠው ወጡ እንጂ፣ በአልማ ሥምና በልማት ሰበብ የተሰበሰበን የህዝብ ገንዘብ በአሜሪካ ባንኮች ውስጥ ለመደበቅ የተላከ መልዕክተኛ መሆኔን በአንድ አዳራሽ ለተገኙት አንድ ሺህ ያህል ተሰብሳቢዎች በአዋጅ የነገሩና ያምኑላቸው ዘንድ አበክረው የተማጠኑም ነበሩ።

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፣ ከብዙ ግለሰቦች ጋርም የአልማን መመሥረት አንስተን ተወያይተናል። ከእነዚህ አንዱም የትጥቅ ትግሉ ግማሽ መንገድ ድረስ የኢሕዴን /የአሁኑ በአዴን/ ታጋይ የነበረና ትግሉ ያስተዋወቀን የቀድሞ ወዳጄ ነው። የአልማን መመሥረትና ዓላማውን ላስረዳው ስሞክር ብዙ የመናገር እድል አልሰጠኝም። ‹‹እናንተ ሰዎች! ጤነኞች ናችሁ!?›› ሲል ጮኸብኝ። እንዳልገባኝ ገለፅኩለትና የጤናችን መጓደል የቱ ላይ እንደሆነ እንዲያብራራልኝ ጠየቅሁት።

‹‹ጤነኞች አይደላችሁም። አብዳችኋል። አማራ አቀፍ ልማት ማህበር የሚሉት መመስረታችሁን እንዴት ከመልካም ቆጥረህ ልትነግረኝ ትሞክራለህ? ፖለቲካውን በጎሳ! አስተዳደሩን በጎሳ! አሁን ደግሞ ልማቱን በጎሳ! አገር የመበጣጠል አባዜያችሁ የፈጠረው የጥፋት



የአልማ ችግኝ ማፊያ ጣቢያ ለአንግረብ ተፋሰስ ልማት (ጎንደር)



የባህር ዳረር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የአልማ አባላት በችግኝ ተከላ ላይ

‹‹ውሃ የለም እንጂ ውሃ በነበር፣
አዬ አገር አዬ አገር አዬ አገር ጎንደር፡

የአገራችን አዝማሪ በጎንደርኛ ዘይቤ ሲያቀነቅን ለአንዴም ሳይቋጥር የማይዘላቸው፣ ድፍን የጎንደር ከተማ ሕዝብም ለዘመናት ያንጎራጎራቸው የብሶት ስንኞች ነበሩ።

ለዚህ ብሶት መነሻ የሆነው የጎንደር ከተማ የንፁሕ የመጠጥ ውሃ ችግር ለብዙ ዓመታት ከዘለቀ በኋላ የተሟላ ተግባራዊ ምላሽ ያገኘው ከ1986 ዓ.ም በኋላ ነው። በእርግጥ፣ በአሁኑ ጊዜ ለጎንደር ከተማ ሕዝብ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የተገነባው የአንገረብ ወንዝ ግድብ ሥራ የተጀመረው በደርግ ዘመነ መንግሥት ነበር።


ይሁን እንጂ፣ ያለፈው መንግሥት ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ የግድቡን ግንባታ ሊያጠናቅቀው ካለመቻሉም በላይ፣ የኢሕአዴግ መንግሥት ይህን ውዝፍ ፕሮጀክት የተረከበው ከበርካታ ችግሮቹ ጋር ነው። ሕዝቡ ‹‹ለአንገረብ ግድብ የወጣው ገንዘብ ቢከመር ራሱ ግድብ መሆን በቻለ ነበር፤ ለዚህ ግድብ ሥራ የተሰማሩት የበሉት በግም አጥንቱ የግድቡን ዙሪያ ማጠር ይችላል›› ሲል በፕሮጀክቱ ሠራተኞች ላይ መሳለቁም ይነገራል።

ለግድቡ አለመጠናቀቅ ዋነኛው ችግር በአንድ ክረምት ዝናብ በደለል እየተሞላ፣ የየዓመቱ የደርግ መንግሥት ዕቅድም ደለል መጥረግ ሊሆን በመገደዱ ነበር።

ከደርግ መውደቅ በኋላ ግን የአንገረብ ግድብ ሥራ በልዩ ትኩረትና በአዲስ መልክ ተከናውኖ የጎንደር ከተማ ሕዝብ የንፁህ የመጠጥ ውሃ ችግር ሊፈታ ችሏል። ፕሮጀክቱን ለመልካም ፍፃሜ ያበቃውም መንግስት የግንባታውን ሥራ ሲሰራ፣ አማራ አቀፍ ልማት ማበር (አልማ) ደግሞ ወደ ግድቡ የሚገባውን ደለል መከላከል የሚያስችል የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ማከናወን በመቻሉ ነው።



# ‹‹...አዬ አገር ጎንደር››





# የጎንደር ከተማ ነዋሪዎችና የዙሪያው ገጠሮች አርሶ አደሮች በአልማ ተደራጅተው በዛፍ ተከላና በእርከን ሥራ ያለሙት የአንገረብ ተፋሰስ (ጎንደር)

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር ከፍተኛ በጀት በመመደብና የጎንደር ከተማ ነዋሪዎችንና በወንዙ ተፋሰስ ዙሪያ የሚኖሩ አርሶ አደሮችን በማስተባበር ከ9ሺ ሄክታር በላይ የተፋሰሱ መሬት ላይ የዛፍ ችግኝ እንዲተከልና እርከን እንዲሰራ አድርጓል። ይህ የረዥም ጊዜ ክትትል ሳይለየው በአልማ የተከናወነ የተፋሰስ ልማት ወደ ግድቡ ሊገባ የሚችለውን ደለል በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንስ በመቻሉ፣ ግድቡ ዛሬም ድረስ አገለግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የዚህ መፅሔት ዝግጅት ክፍል ባልደረቦችም የአንገረብ ግድብ የተፋሰስ ልማት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመታዘብ ወደ ጎንደር ተጉዘን የሆነውን ሁሉ በዓይናችን ልንመለከት ችለናል።

በዚህም መሠረት፣ አንድ ኮረብታ ላይ ወጥተን አንገረብ ወንዝን ከግራና ከቀኝ ያጀቡትን ሰንሰለታማ ተራሮችና ተዳፋት መሬቶች ቃኘን። አልፎ አልፎ ከሚታዩትና የእርከን ክትር ከበዛባቸው ጥቂት ኪስ መሬቶች በስተቀር፣ አብዛኛው ምድር በአረንጓዴ ዛፎች ተሸፍኗል። ወደ ስፍራው የተጓዝነው ጫን ባለው የክረምት ወቅት፣ የሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ ስለነበር፣ የልምላሜው ውበት ዓይንን ያማልላል። አንገረብ ወንዝም የደን ውስጥ ተጓዥ መሆን በመቻሉ፣ በረዥሙ ተዘርግቶ አይታይም።

የቆምንበት ኮረብታ ላይ ያገኘናቸው አንድ የጎንደር ከተማ ነዋሪ አባትም፣ ከቀድሞ የተራቆተ ገፅታው ጋር እያነፃፀሩ የተፋሰሱን ልማት ታላቅነት ተረኩልን። በማስከተልም፣ ‹‹አንገረብ ወንዝን ስናውቀው እንዲህ አልነበረም፣ የሚያስገርም ነገር እያየንበት ነው›› አሉን።

ምን አስገራሚ ነገር እንዳዩበት እንዲነግሩን ጠየቅናቸው ‹‹ተመልከቱ፣ አሁን ጭፍን ያለው የሐምሌ ክረምት ላይ ነን። እንዲህ በመሰለው ከብዶ በጠቆረ ክረምት አንገረብ አተላ መስሎ ይደፈርሳል፤ ይጎሻል እንጂ የጠራ ውሃ አይፈስበትም። ዛሬ ግን በዋናው ክረምት፣ በሐምሌ ምድር የበጋ ውሃን መስሎ የኮለለ ንፁሕ ውሃ ሲወርድበት ማየታችን በጣሙን የሚያስገርም ነው›› ነበር ያሉን።




‹‹እንገሬብ ወንዝን ስናውቀው
እንዲህ አልነበሬም፣
የሚያስገርም ነገር
እያየንበት ነው››



*ታዳጊ ሰለሞን ወርቁ*

እኛም ሌሊቱን ኃይለኛ ዝናብ ጥሎ እንደነበር እያስታወስን፣ ወደ ወንዙ ወርደን የሐምሌ ውሃውን አየን። በእርግጥም የጠረረ ሃጋይ ውሃን ይመስላል።

ከጎንደር ከተማ በስተምዕራብ ዳርቻ በኩል የሚያልፈውን አንገረብ ወንዝና ሰፊ የተፋሰስ ልማቱን ጎብኝተን ስንመለስ ደግሞ መገጭ ላይ ቆምን። መገጭ ከከተማዋ በስተምሥራቅ በኩል በቅርብ ርቀት የሚያልፍ ሌላ ወንዝ ነው።

ሰለሞን ወርቁ የ15 ዓመት ታዳጊ ነው። በመገጭ ወንዝ ዳርቻ የቤተሰቦቹን የበቆሎ አዝመራ ሲጠብቅ ነበር ያገኘነው። ለታዳጊ ሰለሞን ወርቁ ያቀረብንለት ጥያቄ ባላዋቂነት ወይም በሌላ ጎደሎነት እንዳስገመተን ከመልስ አሰጣጡ ያስታውቅ ነበር።

እንዲህ ነበር ንግግራችን፦
እኛ፦ ‹‹ይህ ወንዝ ማን ይባላል?››
ሰለሞን፦ ‹‹መገጭ። ››
እኛ፦ ‹‹መገጭ የሚጠራው መቼ ነው?››
ሰለሞን፦ ‹‹እንዴት ያለ ጥያቄ ነው?!››
እኛ፦ ‹‹የመገጭ ድፍርስ ውሃ የሚጠራው መቼ ነው?››
ሰለሞን፦ (ከመገረም ጉርምርምታና ከትንሽ ዝምታ በኋላ) ‹‹በበጋው ነዋ?!››
እኛ፦ ‹‹በክረምት የጠራ ውሃ አይወርድበትም?››
ሰለሞን፦ ‹‹ ምን ሁናችኋል?! መገጭ እንዴት ብሎ በክረምት ሊጠራ ይችላል?!››

የጎንደሩ አባት እነደነገሩን፣ የድሮው አንገረብም ክረምቱን ጉሽ የአፈር ጠላ እንደመሰለ ደፍርሶ የሚከርም፣ ያለ በጋ የማይጠራ ነበረ። መገጭ ግን እንደ አዲሱ አንገረብ ኩል አይመስልም። ጥንትም ሆነ ዛሬ አንድ ዓይነት ነው። ሰማዩ ሲዳምን ይጎፍራል፣ እንቆቆ ይሆናል። ሰማዩ ሲጠራና ጀንበር ስትጠር ጎፈሬውን ላጭቶ አሰር የሌለው ጠለላ ይሆናል።

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የጎንደር ከተማ ነዋሪዎችንና የዙሪያውን አርሶ አደር አስተባብሮ ተፋሰሱን ችግኝ ባይተክልበትና እርከን ባይከትርበት ኖሮ፣ ይህን ጊዜ አንገረብም መገጭን ነበር። መገጭም ግድብ ሊሰራበት ነው አሉ። ግድቡ ግን የውሃ ጋን እንጂ የአፈር ቋት እንዳይሆን በተፋሰሱ ላይ የአፈር ጥበቃ ልማት ሊከናወንበት ይገባል። የሚያለማውም ራሱ የጎንደርና የአካባቢው ሕዝብ በመሪ እየተመራና ተደራጅቶ ብቻ ነው።


‹‹ምን ሁናችኋል?!
ሠገጭ እንዴት ብሎ በክረምት
ሲጠራ ይችላል?!››